# በውሃ ፍጆታ ክፍያዎ ላይ ገንዘብ መቆጠብ ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

ነዋሪዎች በወርሃዊ የውሃ ፍጆታ ክፍያቸው ላይ ከ**$15-$65 ቅናሽ** ያገኛሉ። እኛ— የዲሲ መንግስት— ክፍያዎችን በመቀነስና ለተጠቀሙት ውሃ ክፍያ ይህን ቅናሽ ለነዋሪዎች አቅርበናል። የእርስዎ ቅናሽ የሚሰላው በቤተሰብዎ ገቢ ላይ ተመስርቶ ነው። ድጋፍ አግኝቶ ለመቀጠል በየአመቱ ሴፕቴምበር ላይ እንደገና ማመልከት ይኖርብዎታል።

ይህ ፕሮግራም Clean Rivers Impervious Area Charge (CRIAC፣ የንጹህ ወንዞች የማይበላሽ የአካባቢ ክፍያ) የነዋሪዎች የእርዳታ ፕሮግራም ይባላል እናም የቀረበው በ Department of Energy and Environment (ሃይልና አካባቢ መምሪያ) ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያጣሩ።

ብቁ የሚሆኑት እነዚህ መግለጫዎች **በሙሉ** እውነት ሲሆኑ ነው።

- ዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ።
- በእርስዎ የዲሲ ክፍያ ላይ ስምዎ ወይም በቤተሰብዎ ውስጥ የሚገኝ የሆነ ሰው ስም ከተዘረዘረ። ይህ ካልሆነ፣ በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ የሆነ ሰው የቤትዎ ባለቤት እንደሆነ ወይም የቤትዎን የዲሲ ውሃ ክፍያ ለመክፈል ሃላፊነቱን እንደወሰደ ማሳየት አለበት።

እንዲሁም ከእነዚህ መግለጫዎች **አንዱ** እውነት ከሆነ፡

- ቤተሰብዎ ከእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ ቢያንስ በአንዱ ድጋፍ የሚያገኝ ከሆነ፡ ተጨማሪ የምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፣ ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጥ ጊዜያዊ ድጋፍ (TANF) ወይም የተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI)። ***ወይም***
- የቤተሰብዎ አመታዊ አጠቃላይ ገቢ —ታክሶችን ከመክፈልዎ በፊት ያለው የእርስዎ ገቢ— በቤተሰብዎ መጠን ላይ ተመስርቶ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች ነው። የቤተሰብ ገቢዎን ለማስላት፣ ከእርስዎ ጋር አብረው የሚኖሩ አዋቂዎች ስራ በመስራት ገቢ የሚያገኙትን ገንዘብ ይደምሩ፡፡ ከዚያ፣ ከ18 አመት በታች ያሉትን

ልጆች አጠቃልሎ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ከማህበራዊ ዋስትና፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም የጡረታ ክፍያዎች የሚያገኘውን ገንዘብ ይደምሩ። ለማወቅ ከስር ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| **የቤተሰብ መጠን**(ከ እርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | **በየወሩ $65 ቅናሽ** ~ለማግኘት የሚኖረው ከፍተኛ የቤተሰብ ገቢ | **በየወሩ $45 ቅናሽ** ~ለማግኘት የሚኖረው ከፍተኛ የቤተሰብ ገቢ | **በየወሩ $15 ቅናሽ** ~ለማግኘት የሚኖረው ከፍተኛ የቤተሰብ ገቢ |
|---|---|---|---|
| 1 | $37,575 | $70,600 | $88,200 |
| 2 | $49,137 | $80,650 | $100,800 |
| 3 | $60,698 | $90,750 | $113,400 |
| 4 | $72,260 | $100,800 | $126,000 |
| 5 | $83,822 | $110,900 | $126,000 |
| 6 | $95,383 | $121,000 | $126,000 |
| 7 | $97,551 | $126,000 | $126,000 |
| 8 | $99,719 | $126,000 | $126,000 |

# ያመልክቱ።

**ለእርስዎና በቤትዎ ውስጥ ለሚኖር ለእያንዳንዱ ሰው** የሚከተሉትን ሰነዶች ይሰብስቡ። ቢያንስ በአንዱ ሰነድዎ ላይ የእርስዎ ሙሉ ስም መዘርዘር አለበት እንዲሁም እርስዎ በዲሲ ውስጥ እንደሚኖሩ ለማሳየት የዲሲ አድራሻ መኖር አለበት። እንዴት እንደሚያመለክቱ ባለው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ፣ ሰነዶችዎን ኮፒ ማድረግ ወይም ስካን ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል።

- ፎቶ ያላቸው መታወቂያዎች (እንደ መንጃ ፈቃድ ያሉ)
- የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች ወይም የውጪ ዜጋ የምዝገባ ቁጥሮች

- በጣም የቅርብ ጊዜ የውሃ ክፍያዎች
- የቅርብ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትና መግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም የታክስ ተመላሾች (ለእርስዎ የሚሆን ሁኔታ ጋር የሚተገበሩ ሰነዶች ብቻ ያስፈልጉዎታል)

በኦንላይን ወይም በፓስታ መልእክት ለማመልከት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ይምረጡ፡

- **የኦንላይን ማመልከቻውን** ይሙሉ። ለመጀመር በመለያ መግቢያ እንዲፈጥሩ ይጠየቃሉ። የንጹህ ወንዞች የማይበላሽ የአካባቢ ክፍያ (CRIAC) የነዋሪዎች የእርዳታ ፕሮግራም ላይ ፍላጎት እንዳለዎት ይምረጡ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ማመልከቻው እንዲሰቅሉ ያስፈልጋል።

- በኢሜይል ለማመልከት የተጠናቀቀውን የ**ፒዲኤፍ ማመልከቻ** ለ criac.residential@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ኢሜይሉ እንዲያያይዙ ያስፈልጋል።

- በፖስታ መልእክት ለማመልከት፣ከዶክመንቶችዎ ቅጂዎች ጋር አንድ ላይ በማድረግ ያጠናቀቁትን **የወረቀት ማመልከቻ** ፕሪንት አድርጎ ከዚህ በታች በተቀመጠው አድራሻ በኩል መላክ። ማመልከቻውን ፕሪንት ማድረግ የማይችሉ ከሆነ፣ በማንኛውም ሰዓት በ311 ላይ በመደወል ማመልከቻዎን እንድንልክልዎት ሊጠይቁን ይችላሉ። ሰነዶችዎን ኮፒ ማድረግ ይኖርብዎታል። እባክዎ ኦሪጂናል ሰነዶች አይላኩ።

Attn፡ CRIAC Residential Relief Program
The Department of Energy & Environment
810 1st Street NE, 9th Floor
Washington, DC 20002

በማንኛውም ጊዜ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

1. ባመለከቱ በሁለት ቀናት ውስጥ እኛ —የዲሲ መንግስት—እርስዎ ተቀባይነት ካገኙ በስልክ ወይም በኢሜይል እንነግርዎታለን። በዚህ ሰአት፣ ምን ያህል ቅናሽ እንደሚያገኙ እናሳውቅዎታለን። በተጨማሪም በማመልከቻው ዙሪያ አዲስ ነገር እንዳለ ለማወቅ፣ በ 311 ላይ መደወል ይችላሉ።

2. ማመልከቻ ካቀረቡበት ጊዜ አንስቶ በሁለት የሂሳብ አከፋፈል ዙሮች ውስጥ (ከሁለት ወር በኋላ) የዲሲ የውሃ ክፍያ ቅናሽ ይመለከታሉ። ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ ወጪዎችን ይሸፍናሉ።

ተቀባይነት ካላገኙ፣ በስልክ ወይም በኢሜይል ካመለከቱበት ቀን በኋላ ባሉት በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን። እኛ ስህተት ስርተናል ብለው ካሰቡ፣ በውሳኔያችን ላይ እንዴት ይግባኝ እንደሚጠይቁ እንገልጽልዎታለን። በተጨማሪም በማመልከቻው ዙሪያ አዲስ ነገር እንዳለ ለማወቅ፣ በ311 ላይ መደወል ይችላሉ።

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች ቅናሽ ያገኛሉ?

አይ፣ የገንዘብ ድጋፉ የሚሰጠው ቀድሞ የመጣ፣ ቀድሞ ይስተናገዳል በሚለው አሰራር ነው። ይህ ፕሮግራም የተከፈተው በጃንዋሪ 2019 ነው፣ ስለዚህ ምን ያህል ነዋሪዎች እንደሚያመለክቱ ወይም የገንዘብ ድጋፉን እንደሚቀበሉ አናውቅም።

## ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

በውሃ ክፍያዎ ላይ ቅናሽ ማግኘትዎን እንዲቀጥሉ፣ በየአመቱ አክቶበር ላይ ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት አለብዎት። አክቶበር ላይ ካላመለከቱ፣ ለእርስዎ የሚሰጠው ድጋፍ ዳግም እስኪያመለክቱ ድረስ ይቆማል። እኛ —የዲሲ መንግስት— በየአመቱ ሴፕቴምበር ላይ እንደገና እንዲያመለክቱ፣ ማመልከቻ በፖስታ እንልክልዎታለን። ከላይ ያሉትን መመሪያዎች በመከተል በአካል መጥተው ወይም በኦንላይን ወይም የማመልከቻ ወረቀቱን በፖስታ ወደእኛ መልሰው በመላክ ዳግም ማመልከት ይችላሉ።

Department of Energy & Environment
810 1st Street NE, 9th Floor
Washington, DC 20002

እንደገና ሲያመለክቱ፣ የቤተሰብዎን ፎቶ ያለባቸው መታወቂያዎች (እንደ መንጃ ፈቃድ ያለ)፣ የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች ወይም የውጪ ዜጋ የምዝገባ ቁጥሮች እና በጣም የቅርብ የውሃ ክፍያ ቅጂዎችን ያካትቱ። በተጨማሪም የቤተሰብዎን ገቢ ማረጋገጫ ያስፈልግዎታል ይህም የቅርብ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትና መግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም የእርስዎ ቤተሰቦችን የታክስ ተመላሾች ሊያጠቃልል ይችላል። በዲሲ ውስጥ እየኖሩ እንደሆነ ለማሳየት፣ ቢያንስ ከሰነዶችዎ አንዱ የእርስዎን ሙሉ ስም እና የዲሲ አድራሻ ማሳየት አለበት።

## ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ በገጹ የታችኛው ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ። አሁንም ድረስ ጥያቄዎች ካለዎት፣ የእኛን የተመጣጣኝነትና ውጤታማነት ቡድንን ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm በ (202) 350-9649 ላይ ደውለው ያግኙን። ወይም በcriac.residential@dc.gov ላይ በርዕሰ መስመር "CRIAC Application Question" በሚል ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

## በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በእኛ የ ፍጆታ ሀብቶች ገጽ ላይ ስለሌላ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የንጹህ ወንዞች የማይበላሽ የአካባቢ ክፍያ (CRIAC) የነዋሪዎች የእርዳታ ፕሮግራምን ከሌሎች ፍጆታ ፕሮግራሞች ጋር መጠቀም እችላለሁ?

አዎ። ሲያመለክቱ፣ የቤትዎን ሙቀትና ኤሌክትሪክ አጠቃቀም ለመቀነስ እንዲሁም/ወይም የተበላሸ ማሞቂያ ወይም ማቀዝቀዣ መሳሪያ ለመተካት እርዳታ መግኘት እንደሚፈልጉ መናገር ይችላሉ እንዲሁም/ወይም የፍጆታ ክፍያዎችን ለመርዳት ፈቃድ ካገኙ፣ ለእነዚህ ፕሮግራሞች እንዴት እንደሚያመለክቱ በመግለጽ በሁለት የስራ

ቀናት ውስጥ ኢሜይል እናደርግልዎታለን። በተጨማሪም፣ የፍጆታ ድጋፍ ቀድመው ካገኙ፣ ለውሃ ክፍያዎ ቅናሾች ወዲያውኑ ተመዝግበው ሊሆን ይችላል። ቀድሞውኑ ቅናሾችን እያገኙ እንደሆነ ለማየት የውሃ ክፍያዎችዎን ይፈትሹ።

## የሚቀበሉትን የቅናሽ መጠን የሚወስነው ምንድን ነው?

ቅናሹ በቤተሰብዎ መጠንና በአመታዊ ጠቅላላ ገቢ - ያ ማለት ታክሶችን ከመክፈል በፊት ያለ የእርስዎ ገቢ ላይ ይመሰረታል።

## በኮቪድ-19 የህዝብ ጤና ድንገተኛ ጊዜ ላይ በመሆኑ የውሃ ክፍያዬን አዘግይቻለሁ። መዘጋትን ለማስቀረት ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት እችላለሁ?

ይህ ጊዜ ለነዋሪዎች ከባድ እንደሆነ እናውቃለን። እርስዎ የንጹህ ወንዞች የማይበላሽ አካባቢ ክፍያ (CRIAC) የነዋሪዎች የእርዳታ ፕሮግራም እየተቀበሉ ከሆነ በኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) የህዝብ ጤና ድንገተኛ ጊዜ ያልተከፈሉ የዲሲ የውሃ ክፍያዎችንና የድንገተኛ ጊዜው ካለቀ በኋላ ባሉት 105 ቀናት ወጪ ለመሸፈን እስከ 2,000 ለሚሆን ክሬዲት በተጨማሪ ብቁ ነዎት። ይህንን ክሬዲት ለእርስዎ ወዲያው ተግባራዊ እናደርገዋለን።

## የውሃ ክፍያው በቤቴ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም ሰው ስም አይደለም። አሁንም ማመልከት እችላለሁ?

አዎ፣ አሁንም ቢሆን ማመልከት ይችላሉ። የእርስዎ የዲሲ ውሃ ፍጆታ የቤተሰብ አባልን ስም የማይዘረዝር ከሆነ፣ ከቤተሰብዎ ውስጥ የሆነ ሰው የቤትዎ ባለቤት እንደሆነ የሚያሳይ ወይም ከቤተሰብዎ ውስጥ ያለ ሰው ለእርስዎ የዲሲ ውሃ ፍጆታ ክፍያዎች ሃላፊነቱን እንደወሰደ የሚገልጽ የኪራይ ውል ቅጂ ማካተት አለብዎት።

## ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?

እርስዎ ለቅናሹ ተቀባይነት እንዲያገኙ በቤተሰብዎ መጠን ላይ የተመሰረቱ ገደቦች ጋር ገቢዎ እኩል ወይም በታች መሆን አለበት። በአካል ወይም በኦንላይን ማመልከቻ

ካመለከቱ እና በኋላ ላይ የገቢ መስፈርቶቹ ከተቀየሩ፣ ማመልከቻዎ እንደገና ሊገመገም ይችላል። ያን ጊዜ ብቁ ከሆኑ፣ ወዲያውኑ ቅናሹን ያገኛሉ።

## እኔ በዲሲ ውስጥ ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት እመራለሁ። በእኛ የውሃ ክፍያ ላይ ቅናሽ ልናገኝ እንችላለን?

አዎ! እንደ **CRIAC ለትርፍ የማይሰራ የእርዳታ ፕሮግራም** ክፍል፣ በውሃ ክፍያዎ ላይ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለ ማመልከቻውና የብቁነት መስፈርቶች ለማወቅ ማገናኛውን ይከተሉ።

## ቤተሰቤ ምንም አይነት ገቢ የለውም። ያንን እንዴት ላስረዳ እችላለሁ?

ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ የሌለው ከሆነ፣ ከማመልከቻዎ ጋር**ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሰነድ ማስገባት ይችላሉ፡**

- በውል አዋዋይ ባለስልጣን የተረጋገጠ **የትርፍና ኪሳራ መግለጫ**፣
- በ Department of Employment Services (DOES፣ ቅጥር አገልግሎቶች ክፍል) ድረ ገጽ “ቀሪ” ሂሳብዎ ዜሮ እንደሆነ የሚያሳይ የእርስዎ “ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መግለጫ” ቅጽበታዊ ገጽ እይታ**(ምሳሌውን ይመልከቱ)**፣
- ከቀድሞ አሠሪዎ ከአሁን በኋላ እዚያ እንደማይሠሩ የሚገልጽ ደብዳቤ (ከስራ ከለቀቁ ግን እስካሁን ድረስ የሥራ አጥነት ጥቅሞችን በ DOES እያገኙ ካልሆነ) ፣ **ወይም**
- ከ District of Columbia Housing Authority (DCHA፣ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን) የመጣው ደብዳቤ የሚገልጸው ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ እንደሌለው ነው።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*